# የቤ/ጉ/ክ/መ/ማ/ቤቶች ኮሚሽን የተሻሻለው የውስጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀም መመሪያ ቁ/3/ 2017 ዓ/ም

## መግቢያ

**የቤ/ጉ/ክ/መ/ መረሚያ ኮሚሽን የተሸሻለ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር ------**

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት በህግ የተሰጡት ተልዕኮ ለማሳካት በዋናነት ከሚያከነውናቸው ተግባራት መካከል የታራሚ ማረም ማነፅ ስራ አንዱ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ከሚከናወኑ ስራዎች የሚመነጨውን ሀበት በአግባቡ ለማሰባሰብና ለማስተዳደር እንዲያስችል በ2004 ዓ/ም በመመሪያ ቁጥር ----- መሰረት የውስጥ ገቢ አሰባሰብ አጠቃቀም ወጦ የገቢ አሰባሰብ ተግባራዊ ሲደረግ ከቆየ በኃል

በ2012 ዓም የገቢ አሰባሰብ አጠቃቀም ስርዓቱን በውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ታስቦ መመረያውን እንደገና በማሻሻያ በመመሪያ ቁጥር ቁ/2/2012 ወጦ ተግባራዊ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን በአዲስ መልክ ተሻሽለው የወጣ መመሪያ ላይ የታየውን የተፈፃሚነቱ ክፍተቶችን በማሻሻልበሁሉም ዘንድ ተፈፃሚነት ያለው የውስጥ ገቢ አሰባሰብን አጠቃቀም ስርዓት በመዘርጋት ገቢውን በአግባቡ በማስተዳደር በራስ አቅም ተቋማዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትበበለጠ እንዲሻሻል የውስጥ ገቢ አሰባሰብ አጠቃቀም ስርዓት የግልፅነትና የተጠያቂነት ባለው አሰራር እንዲመራ ይህ የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም መመሪያ እንደገና ተሻሽሎ ውጥቷል

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1.አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ‹‹የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን የተሻሻለው የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 3/2016 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2.መመሪያ የማወጣት /አውጪው/ ባለስልጣን

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ስልጣንና ተግባሩን ለመወሰን እንደገና ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 186/2014 አንቀጽ 72 በን/ቁ 2 ለኮሚሽኑ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አሻሽሎ አውጥቷል ፡፡

## 3.ትርጓሜ፣

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

3.1 **የውስጥ ገቢ**"ማለት፣ በታራሚ ማረም ማነፅ ሂደት ከተለያዩ የግብርና ልማት ስራ፤ ከልዩ ልዩ የእደ ጥበብ ስራ ውጤቶች ሽያጮች እና ከልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍያ በማናቸውም ዓይነት በማረሚያ ቤት ገቢ ከሚያስገኙ ስራዎች የሚገኝ ገንዘብ ጥሬ ዕቃ ።

3.2. **የግብርና ምርት**››ማለት በኮሚሽኑ ስር ባሉ ማረሚያ ቤቶች በህግ ታራሚዎች የሚመረቱ የሰብል ልማት፤ እንስሳትና የእንስሳት ተዋፅኦ ምርት ውጤቶች ።

3.3.‹‹**የኢንዱስትሪ ምርት**››ማለት በኮሚሽኑ ስር ባሉ ማረሚያ ቤቶች መምሪያ በተዘጋጀው ማምረቻ ወርክ ሾፕ ውስጥ የሚመረቱ የሚመረቱ የምርት ውጤቶች

3.4.‹‹**በትምህርትና ስልጠና ሂደት የሚመረቱ ምርቶች** ›› ማለት በኮሚሽኑበዞን ማረሚያ ቤቶች መምሪያ ለታራሚዎች በሚሰጡ የሙያ ክህሎት ስልጠና ሂደት የሚመረቱ ምርቶች ውጤቶች ።

3.5.‹‹**የምርት ተጠቃሚ**››ማለት በማረሚያ ቤቱ የሚመረቱ ምርቶችን በመግዛት ተጠቃም የሆኑ የህብረተሰብ ክፍል ፡

3.6.‹‹ **የማረሚያ ቤት ማህበረሰብ**›› ማለት ተቋማዊ ዓለማ ለማሳካት የተመደቡ የፖሊስ አባላት ስቨል ባለሙያዎች በልዩ ልዩ ስራ መስክ ጊዜያዊ ፤በፍርድ ቤት የተላለፈባቸውን ፍርድ ለመፈፀም በእርምት ላይ የሚገኙ ታራሚዎች ።

3.7.‹‹**የምርት ግብዓቶች**›› ማለት በየማረሚያ ቤቱ ለሚካሄደው የልማት ስራ ምርት ማከናወኛ የሚያስፈልጉ አቅርቦቶች ማለት ነው።

3.8.‹‹**የግብይት ስርዓት** ›› ማለት ተስማሚ በሆኑ በማንኛውም ዘዴዎች ስለአሻሻጥ ለግኘዎች መረጃ የሚተላለፍበት ሽያጭና ገዥ የሚገለገልበት ዘዴ ማለት ነው።

3.9.‹‹**የውስጥ ገቢ ደረሰኝ**ማለት፣ማረሚያ ቤቶች የውስጥ ገቢ ለመሰብሰብ በክልሉ ፋይናንስቢሮ ዕውቅና ታተሞ በሚወጣ መነሻና መድረሻ ቁጥር ያለው ደረሰኝ የገቢ መሰሰብሰቢያ ደረሰኝ ነው

## 4.የውስጥ ገቢ መመሪያው አስፈላጊነት፣

ይህ የማረሚያ ቤቶች የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም መመሪያ እንዲወጣ ያስፈለገው በሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው።

4.1.በታራሚ ማረም ማነፅ ሂደት ከማረሚያ ቤት የሚመነጨውን ሀብት በአግባቡ በማሰባሰብና በማስተዳደር ሀብቱን ትርጉም ባለው መንገድ ስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ

4.2.የተቋሙን የማረምና የማስተማር የማቋቋም ተግባር ተልዕኮ በተሻለ መንገድ ለመፈፀም፣

4.3.በማረሚያ ቤቶች የሚገኘውን የሰው ጉልበትና እውቀት በስራ ፈጠራላይ በማዋል ሀብት የማመንጨት አቅም ማሳደግ

4.4..የማረሚያ ቤቶች የውስጥ ገቢ በማሳደግ የተሻለ ገቢ በመሰብሰብ በመንግስት ወጪ ሊሸፈኑ የማይችሉ የማረሚያ ቤቶችን የውስጥ ችግሮች ለማቃቀል

## 5. የመመሪያ ዓላማ

### 5.1 ጠቅላላ ዓላማ ፡-

ከማረሚያ የሚሰበሰብ ገቢ አመራር ስርዓት ግልፅ ፤ተጠያቂነት፤ ፍትሃዊ በሆነ አግባብ በማስተዳደር የታራሚ ማረም ማነፅ ስራ ጥራት ተደራሽነት ፤የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት የተደራሽነት ችግር በመፍታት የታራሚ ማረም ማነፅ የማስተማር ፤የስልጠና የፈጠራ ክህሎት ማሻሻያ ማዕከላት አደረጃጀት በማሻሻል የተቋሙን ተልዕኮ አፈፃፀም ውጤታማነት ማሳደግ

### 5.2. ዝርዝር ዓላማ

ሀ..በታራሚ ማረም ማነፅ ሂደት ከተቋሙ የሚመነጭ ሀብት በአግባቡ በማሰባሰብና በማስተዳደር በሀብት ውስንነት መፍታት ያልተቻሉ የተቋሙ የውስጥ ችግሮችን በራስ አቅም በመፍታት የተልዕኮ አፈፃፀም ውጤታማነት ማሻሻል

ለ.በውስጥ ገቢውየታራሚ ማረም ማነፅ የማስተማር ፤የፈጠራ ክህሎት ማሻሻያ ማዕከላት በማቋቋሚያ ስራ የታራሚውን የአስተሳሰብ የአመለካከት ግንባታ ስርዓት ለማሳደግ

ሐ.ከዞን ማረሚያ ቤት ከሚሰበሰብ ገቢ ከኮሚሽኑን የገቢ ድርሻ የኮሚሽኑ ዋና ዋና ስትራቴጂካዊ ዓላማ ማሳካት የሚያስችሉ ስራዎች ላይ እንዲውሉ ማድረግ

መ. የታራሚውንዕውቀት ጉልበት የፈጠራ ችሎታ በማሳደግ የውስጥ ገቢውን ማሳደግ የሚያስችሉ የስራ መስኮችን በማስፋት የገቢ አቅሙን በማሳደግ የመንግስት በጀት ጠባቂነትን በመቀነስ በራስ አቅም ተቋማዊ ጉድሎቶችን የመፍታት አቅም መፍጠር

## 6.የፈተፃሚነት ወሠን፣

ይህ መመሪያ ተፈፃሚነቱ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ማረሚያ ኮሚሽን እና በስር በሚገኙ የዞን ማረሚያ መምሪያዎች ተፈጻሚ ይሆናል፡

## 7.የውስጥ ገቢ አሰባሰብ መመሪያው መርሆዎች

- አመኔታ ያለው የገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ስርዓት
- ግልፅኝነትና ተጠያቂነትን ያለው የሀብት ብክነትን የመቀነስ አሰራር
- የጋራ መግባባት፤ ቅንጅታዊ፤ፍትሃዊ አሰራር የተከተለስርዓት
- የታራሚ የማረም ማነፅ ውጤታማነት ማሳደግ

# ክፍል ሁለት 2

## 8. ገቢ ስለ መሰብሰብ እና ስለመጠቀም

ሀ.ኮሚሽኑ በአዋጅ ቁጥር 186/2014 አንቀጽ 7 ን/ቁ 11 መሰረት ከተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ገቢ የመሰብሰብና የማስተዳደር  ስልጣን ተሰጥቶታል

ለየክልሉ ማረሚያ ኮሚሽን ከዞን ማረሚያ መምሪያ ከተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራ መስክ የሚሰበሰበው ገቢ በዕቅድ በማስደገፍ የተቋሙን ተልዕከ አፈፃፀምና አገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን በሚያስጠብቁ ስራዎች ላይ እንዲውል ያደረጋል

ሐ.ከተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራ መስክ የሚሰበሰብ ገቢ በክልሉ ፋይናንስ ቢሮ በኩል በሚታተም ህጋዊ የገቢ መሰብሰቢያ  ደረሰኝ ብቻ የሚሰበሰብ ይሆናል ፣

**9.የማረሚያ ቤት የውስጥ ገቢ የገቢ ምንጮችና  እና የገቢ መደቦች**፡- ከማረሚያ ቤት የሚሰበሰብ ገቢ 4 ዋና ዋና የገቢ ምንጭ ስር ከዝርዝር የገቢ ምንጭ ይሰበሰባል

9. የግብርና ልማት ስራ ውጤት

**9.1 ሰብል ልማት** ፡-/የመኸር ሰብል ልማት፤የበጋ መስኖ ልማት፤የቋም አትክልትና ፍራፍሬከጓሮ አትክልት ልማት ምርት ውጤት ሽያጭ የሚሰበሰብ ገቢ፤

**9.2 የእንስሳት ሀብት ልማት** ፡-/ከእንስሳት እርባታ ፤ከደለቡ እንስሳ እናየእንስሳት ተዋጾኦ እና ከንብ ማነብ ስራ የሚገኝ የማር ምርት ሽያጭየሚሰበሰብ ገቢ ሲሆን እነዚህ ገቢዎች በገቢ መደብ /ርዕስ/1455 ስርይመዘገባል፡

**ለ.ከእደ ጥበብ ስራ ውጤት ሽያጮች፡-**

- ከሸማ ስራ ፤ከእንጨት ስራ፣.ከብረታ ብረት ስራ ፣ከቡሎኬት ከጡብ ልዩ ልዩ የእጅ ጥበብ ስራ እና ከዚህ ጋር ተያያዥ ያላቸው ማናቸውም ምርት ውጤት ሽያጭ

**ሐ.ከልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍያ፡-**

- ከተለያዩ የተረፈ ምርት ሽያጭ ፤ከፀጉር ስራ ፣ከሊሲትሮ ስራ ፤ከአዳራሽ ኪራይ ፣ከአረጁ ንብረቶች ሽያጭ፤ለገቢ ማሰባሰቢያ በተዘጋጀ ፕሮግራሞች ከማህበረሰብ በጥሬ ገንዘብና በዓይነት የተገኙ ገቢዎች፤በተቋሙ በኩል ከተለያዩ ተቋማት ጋር በውል ለሚሰሩ የጉልበት ዋጋ ክፍያ የሚቀነስ የአገልግሎት ክፍያ ገቢ ፤ ከተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራ ከሚገኝ ገቢ ከህግ ታራሚዎች የሚሰበሰብ ወርሃዊ የአገልግሎት ክፍያ የሚገኝ ገቢ

**መ..ከቦታና ከቤት ኪራይ ፤**

- ከሻይ ክበብ ፣ከተለያዩ መዝናኛ ክበባት ክራይ ፤ለፀጉር ስራ፣ከህብረት ሱቅ ክራይ ከእርሻ ትራክቴር ክራይ እና ሌሎች ተያያዝ ያላቻው ስራዎች የሚገኝ ገቢ ናቸው

**10. የገቢ ሂሳብ መደብ መለያ ቁጥር** ፡-

ሀ.. ከላይ በቁጥር 2.1፣1 ስር ከተጠቀሰ የገቢ ማስገኛ ስራ ዘርፍ የሚሰበሰብ ገቢ በገቢ መደብ/ርዕስት/ 1455 ስር ይመዘገባል

ለ.ከላይ በቁጥር 2.1.2., 2.1.3 ,2.1.4, ስር ከተጠቀሰ የገቢ ማስገኛ ስራ ዘርፍ የሚሰበሰብ ገቢ በገቢ መደብ/ርዕስት/ 1438 ይመዘገባል፣

**11.የገቢ ክፍፍል ድርሻ**፡-

ከውስጥ ገቢ ስራዎች ከሚሰበሰብገቢ የክልልና የዞን ማረሚያቤት የተጣራ ገቢ ድረሻ ከዚህ በታች ለተጠቀሱ ስራ ዘርፎዎች በፔርሰንት እንዲጠቀሙ ይደረጋል ፡-

ሀ›በዞን ማረሚያ መምሪያ በገቢ ምንጭነት ከተመዘገቡ የስራ ዘርፎች ከሚሰበስቡ የተጣራ ሀብት/ገቢ/ ------ ፐርሴንት/የገቢ ድርሻ በዞን ማረሚያ ቤትበበጀት ዓመቱ በውስጥ ገቢ በጀት ለማከናወን በዕቅድ ለተቀመጡ ተግባራት ማስፈፀሚያ የሚጠቀሙ ሲሆን

ለ.የክልል ማረሚያ ቤት የዞን ማረሚያ ቤት ከሚሰበሰቡት የተጣራ ሀብት /ገቢ /-----ፐርሴንት የገቢ ድርሻ የሚያገኙ ሲሆን ከሚያገኝ የገቢ ድርሻ በኮሚሽኑ የተቀመጡ ስትራቴጂካዊ ዓላማ ማስፈፀሚያ ላይ እንዲውል ይደረጋል

ሐ.የዞን ማረሚያ ቤት መምሪያ የኮሚሽኑ ገቢ ድርሻ ሂሳብ መደብ 1455 እና 1438 ተመዝግቦ ለዚሁ ዓላማ በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ቁጥር በየሩብ ዓመቱ መጨረሻ ለክልሉ ማረሚያ ኮሚሽኑንገቢይደረጋል

12.የበጀት ድርሻ መጠን ፡-

የውስጥ ገቢ በጀት አስተዳደር ስርዓቱ ፍታሃዊናምዘናዊ በሆነ መልኩ ስራ ላይ እንዲውል በውስጥ ገቢ በጀት ለሚሸፈኑ ስራዎች ዘርፎች የበጀት ድርሻ በፐርሴንት ይቀመጣል

ሀ.ለውስጥ ፋስሊት ማሟያ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ዕድሳት ጥገና ስራዎች /በመመሪያው ክፍል ሦስት ቀጥር3.4. ን.ቁ3.4.1 ስር ለተዘረዘሩ ስራዎች ------- %

ለ.ለማረሚ ማነፅ ተግባራትስራ በክፍል 3 ቁጥር 3.4 ን/ቁጥር 3.4.2. ስር ለተዘረዘሩ ስራዎች ----%

ሐ.ለማህበራዊና ሰብዓዊ አግልግሎት ድጋፍ በክፍል 3 ቁጥር 3.4 .ን/ቁ 3.4.3 ስር ለተዘረዘሩ ስራዎች ------ %

መ.ለአስተዳደራዊ ስራዎች በመመሪያ ክፍል 3 ቁጥር 3.4.ን.ቁ 3.4 .4 ስር ለተጠቀሱ

ስራዎች ------- %

ሠ.ለወጭ መጋራት ስራ ክፍል ሦስት ቁጥር 3.6 ፊደል ሠ ስር ለተጠቀሰ ስራ -------%

## ክፍል ሦስት

**13. የውስጥ ገቢ ስለመሰብሰብ ፣ አያያዝ እና አጠቃቀም ፣**

**ሀ/የውስጥ ገቢ አሰባሰብ በዚህ መመሪያ ን/ቁጥር 1 እስከ ን/ቁጥር 5 የተዘረዘሩትንና ሌሎችንም የገቢ አሰባሰብ ሂደቶች መሰረት በማድረግ እንዲሰበሰብ ይደረጋል፡፡**

1. በእለት ገንዘብ ሰብሳቢ ገንዘብ ይሰበሰባል ፣
2. የእለት ገንዘብ ተቀባይ በውስጥ ገቢ ማጠቃለያ ደረሰኝ መዝግቦ ለሂሳብ ክፍል ያቀርባል
3. ሂሳብ ኦፊሰሩም የቀረበውን ዝርዝር ሂሳቡን በማረጋገጥ ወደ ዋና ገንዘብ ያዥ ገንዘቡ መግባቱን ይከታተላል ፣
4. በየደረጃው የሚገኘ የማረሚያ መምሪያዎች በፋይናንስ ቢሮ በኩል ለዚህ ዓላማ በታተሙ ደረሰኞች በኮሚሽኑ በኩል ግዥ ተፈፅመው በሚሰራጭላቸው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብቻገቢ ይሰበስባሉ
5. .ማረሚያ ቤቶች ታትመው የደረሷቸውን የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝለቁጥጥር በሚያመች መልኩ ስራ ላይ እንዲውል የደረጋል
6. የዞን ማረሚያ መምረያ እንዲጠቀሙ ታትሞ የተሰጣቸው ደረሰኞች በአግባቡ ስራ ላይ ስለመዋላቸው ለማረጋገጥ በሚመለከተውወ አካል ሲጠይቅም የደረሰኙን የማቅረብና የማስመርመር ኃላፊነት አለበት
7. የዞን ማረሚያ ቤት ታትሞ ከተሰጡ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች በበጀት ዓመቱ ውስጥ ምን ያህል ስራ ላይ እንደዋለ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የጠራ መረጃ ክልል ማረሚያ ቤት ያሳውቃል

8. በሀጋዊ መንገድ ከታተመ ደረሰኝ ወጭ በማንኛውም ሁኔታ ገቢ የሰበሰበ የተሰበሰበውን ከተቀመጡ አሰራር ወጭ የተጠቀመ አካል ካለ የህጋዊና አስተዳደራዊ የሆነ ተጠያቂነት አለባት

9 የክልል ማረሚያ ኮሚሽን በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ የዞን ማረሚያ መምሪያ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ አጠቃቀም ሂደትን የመከታተል የመቆጣጠር ኃላፊነት አለባት

14./ የውስጥ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ህትመትና አጠቃቀም በዚህ መመሪያ መሰረት ይፈጸማል

1. የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ህትመት በፋይናንስ ቢሮ በኩል ለዚህ ዓላማ በታተሙ ደረሰኞች በኮሚሽኑ በኩል ግዥ ተፈፅመው በሚሰራጭላቸው የገቢ መመሰቢያ ደረሰኝ ብቻ ይሆናል

2.የዞን ማረሚያ ቤቶች ታትመው የደረሷቸውን የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል ።

3.የዞን ማረሚያ ቤት እንዲጠቀሙ ታትሞ የተሰጣቸው ደረሰኞች በአግባቡ ስራ ላይ ስለመዋላቸው ለማረጋገጥበሚመለከተውወ አካል ሲጠይቅም የደረሰኙን የማቅረብና የማስመርመር ኃላፊነት አለበት ፣

4.የክልል ማረሚያ ኮሚሽን በኩል ከክልል ፋይናነስ ቢሮና የዞን ማረሚያ ቤት ታትሞ ከተሰጡ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች በበጀት ዓመቱ ውስጥ ምን ያህል ስራ ላይ እንደዋለ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የጠራ መረጃ ክልል ማረሚያ ቤት ያሳውቃል ፣

5.በሀጋዊመንገድ ከታተመ ደረሰኝ ወጭ በማንኛውም ሁኔታ ገቢ የሰበሰብ የተሰበሰበውን ገቢ ከተቀመጡ አሰራር ወጭ የተጠቀመ አካል ካለ የህጋዊና አስተዳደራዊ የሆነ ተጠያቂነትአለባት

6.የክልል ማረሚያ ኮሚሽን በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ የዞን ማረሚያ መምሪያ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ አጠቃቀም ሂደትን የመከታተል የመቆጣጠር ኃለፊነት አለበት

15./ የተሰበሰበ የውስጥ ገቢ አያያዝ አጠቃቀም ፣

1. የዞን ማረሚያዎችከውስጥ ገቢ በደረሰኝ የተሰበሰበ የገቢ ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ኮሚሽን ያሳውቃሉ ፣
2. ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበ ገቢ በተቋም በገቢከተመዘገበ በኃላ በአቅራቢያ በሚገኝ የመንግስት ባንክ ራሱን በቻለ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ተመዝግቦ እንዲቀመጥ ይደረጋል
3. የዞን ማረሚያ መምሪያ በባንክ የተቀመጠ የውስጥ ገቢ ለመጠቀም ሲፈልጉ ገቢውን በጋራ ለማስተዳደር በተደራጀ የጋራ አመራር ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት በቋም ኃለፊ ወይም ተወካይ በተፈረመ የወጭ ትዕዛዝ በውስጥ ገቢ ገንዘብ ያዥ ስም ገንዘቡን ወጭ በማድረግ መጠቀም ይችላሉ ፣

4. በየበጀት ዓመቱ ዕቅድ መሰረት የዞን ማረሚያ በውስጥ ገቢ ሂደት የተከናወኑ የስራ አፈፃፀም ሪፖረት ከመደበኛ የስራ አፈፃፀም ሪፖረት ጋር ለኮሚሽኑና ሚመለከተው የመንግስት አካል እንድቀርበ ይደረጋል
5. ከባለፈ በጀት ዓመት ተሰብስቦ ስራ ላይ ያልዋለ በበጀት ስኖር በዓመቱ ለመሰብሰብ በተቀመጠ ዕቅድ መሰረት ከሚሰብሰብ ገቢ ጋር በገቢ ሂሳብ በማቅረብ እና በማፅደቅ የመንግስት ፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት መጠቀም ይቻላል ፡፡
6. የዞን ማረሚያ መምሪያዎች በበጀት ዓመቱ የሚሰበሰቡትን ገቢ ታሳቢ በማድረግ በበጀት ዓመቱ በውስጥ ገቢ ለማከናወን በዕቅድ ለተቀመጡ የስራ ዕቅድ የሚያስፈልግ በገቢ ሂሳብ መደብ 1441 በበጀት አርዕስት በመሸንሸን ለኮሚሽኑ ያቀርባሉ
7. ኮሚሽኑ ከዞን ማረሚያ መምሪያ የቀረበትለትን የውስጥ ገቢ በጀት ፍላጎት በበጀት ዓመቱ በውስጥ ገቢ ለማሳካት በማረሚያ ከቀረበ የስራ ዕቅድ እና ከውስጥ ገቢ አሰራር መመሪያ አንፃር በማየት ኮሚሽኑ ውሳኔውን ያሳውቃል/ያፀድቃል፣
8. ለውስጥ ገቢ ስራ የሚፈፀም ማንኛውም ክፍያ ወይም ወጭ ትዕዛዝ በስራ ላይ ባለው የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ ይሆንል ፡፡
9. በገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ የተሰበሰበውን ገንዘብ የገቢ አጠቃቀምና ክፍያ መፈፀም የሚቻለው በውስጥ ገቢ ደረሰኝ ከተለያዩ ምንጮች የተሰበሰበ ገቢ ህጋዊ አሰራሩን ተከትሎ በበጀት አመቱ ፀድቆ ስራ ላይ እንዲውል ሲደረግ ብቻ ነው ፣
10. የዞን ማረሚያ መምሪያዎች በበጀት ዓመቱ በኮሚሽን በኩል ከፀደቀላቸው በጀት በላይ መጠቀም የማይችሉ ሲሆን ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ ተጨማሪ በጀት ለመጠቀም የሚያስችል ሁኔታ ሲያጋጥም መጠቀም የሚችሉ በጀት መኖሩን በማረጋገጥ ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ ተጨማሪበጀት ለመጠቀም የተፈለገበትን ምክንያት በመግለፅ ለኮሚሽኑ ተጨማሪ የበጀት ጥያቄ አቅርቦ በኮሚሽኑ በኩል ስፈቀድላቸው ብቻ ነው

**16./.በማረሚያ ተቋማት በሚሰበሰብ የውስጥ ገቢ በጀት በዋናነት የሚከናወኑ ስራዎች**

**1.ማ/ቤቶች ቅድሚያ ለሚሰጡት ለህግ ታራሚዎች ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ማለትም፣**

ሀ ለታራሚዎች መኖሪያ ቤት ማስፋፊያ ስራና ጥገና ፣

ለ ለመፀዳጃ ቤት ግንባታ ፣ ለሻወር ቤት ግንባታ ፣ ለኤሌክትርክ የወሃ መስመር ጥገኛ

ሐ ለሸንት ቤት መምጠጫና ጽት ፣

መ ለክሊኒክ ጥገናና ማስፋያ ፣

ሠ ለታራሚዎች የመኝታ አገልግሎት የአልጋና ፍራሽ ግዥና ጥገና

ረ አነስተኛ የሆኑ የታራሚ መደሪያ ቤት ጥገኛ ስራ

ሰ.ለታራሚዎች መዝናኛ አግልግሎት የሚውሉ ማቴሪያ ግዥ /ኳስ ፤ቴሌቭዥን /

ሸ/ለሽንት ቤት መምጠጫ መኪና ኪራይና ፣

**17.ለማረም ማነፅ ተሃድሶ ልማትና እና ለሌሎች ተዛማጅ ለሆኑ ተግባራት ማለትም ፣**

ሀ/ ለት/ትና ስልጠና ማዕከላት ማስፋፍያ ግንባታ ዕድሳት ጥገና ፣

ለ/ በቀለም ት/ትና ሙያ ስልጠና ለሚሰማሩ የህግ ታራሚዎች የት/ት ግብዓትና የመማሪያና ስልጠና ቁሳቁሶች ወምበር ጠረጴዛ ፤ኮሚፒዩቴር ፤ፕሪንተር

ሐ/ የስልጠና ማቴሪያል ግዥ /የእንጨት መሰንጠቂያ ፤የቢየዳ ማሽን ፤ ዘመናዊ የሽመና ማሽን ፤የልብስ ስፋት ማሽን

መ/ በማ/ቤቱ ውስጥ የማይገኙ ልዩ የሙያ ስልጠና ሲኖር ታራሚዎችን ለሰልጠኖ ማሰልጠን ወደ ሌላ ማ/ቤት ማዕከል ልኮ ለማሰልጠን የሚያስፈልግ ወጪ መሸፈን ይቻላል ፡፡

ሠ/ ለልማት ማዕከላት ማስፋፍያ ስራ

ረ/ ለልማት ስራ የምርት ግብዓት አቅርቦት ግዥ

ሰ/ የገቢ አቅሙ ስፈቅድ ለግብርና ልማት አገልግሎት የሚውሉ ለማካናይዘሽን ግዥ ስራ

ሸ/ አዳዲስ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ማስፋፍ ያ ስራ ለሚደረጉ ጥናት

**18/ ለአስተዳደራዊ ስራ ወጭዎች**

ሀ/ለጉልበት ዋጋ ክፍያ

ለ/ ለውስጥ ገቢ ስራ አገልግሎት የሚውሉ የስቴሽነር ግዥ

ሐ/ለውስጥ ገቢ ስራ ለሚደረጉ እንቅስቃሴ /የውሎ አባል ፤የትራንስፖርት ክፍያ

መ/ ለውስጥ ገቢ ስራ ለሚውል ነዳጅና ቅባት ግዥ

19.ለህግ ታራሚዎች ማህበራዊ ችግር ፣

ሀ/ በማ/ቤት የሚገኙ ታራሚዎች ሞት ሲገጥማቸው የቀብር ማስፈፀሚያ ወጭ ሸፍኖ የሚረከብ ቤተሰብ ሳይገኝ ስቀር ለቀብር ማስፈፀሚያ የሚውል በጋራ አመራር ኮሚቴ ከውስጥ /ገቢ እስከ 5000/አምስት ሽህ ብር / የሚደርስ ወጭ በመሸፈን የቀብር ስነ ስርዓቱን መፈፀም ይቻላል ፡፡

ለ/ በማ/ቤት ውስጥ እያሉ በጤና መታወክ ፣በዕድሜ መግፋት ምክንያት ሰርተው ገቢ ማግኘት ለማይችሉ ታራሚዎች የአልባሳት ድጋፍ ፤ከማ/ቤት ሲወጡ ከቤተሰቦቻቸው ጋር መቀላቀል እንዲችሉ ለትራንስፖርት ወጪ በጋራ አመራር ኮሚቴ ውሳኔ እስከ 3000 ከውስጥ ገቢ ሊሸፈን ይችላል

ሐ/ ነፍሰ ጡር ሆነው ማ/ቤት ከገቡ በኃላ የሚወልዱ ሴት ታራሚዎች ሲኖሩ ለእናቲቱ እና ለተወለደው /ችው/ህፃን ተጨማሪ የምግብ አቅርቦትና አልባሳት ድጋፍ እስከ 6,000 ብር የገንዘብ ድጋፍ ሊደረግ ይችላል ፡፡

መ/ ከእናታቸው ጋር ማ/ቤት የገቡ ህፃናት እስከ 4000 ብር በሚደረስ ወጭ የንፅህና መጠበቂያ ፣አልባሳትና የመሳሰሉት ድጋፍ

ሠ/ ፍርዳቸው ከአራት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ የህግ ታራሚዎች በማረሚያ ቤቱ ውስጥ በማህበር ተደራጅተው ለመስራት አስበው የገንዘብ እጥረት ካጋጠማቸው በሚያቀርቡት የስራ አዋጭነት ጥናት /ፕሮፖዛል / መሰረት የዞኑ ማረሚያ መምሪያ የበጀት አቅሙን እና አዋጭነቱ ጥናት ውጤታማነት በማመን ለክልሉ ማ/ቤቶች ኮሚሽን ጥያቄ ሲያቀርብ በኮሚሽኑ ውሳኔ የ25 % ድርሻ ብድር ሊሰጣቸው የሚችል ሲሆን የገንዘብ ብድር የተሰጣቸው ታራሚዎች የተበደሩትን ገንዘብ ሳይመልሱ የትርፍ ክፍፍል ማድረግ አይችሉ ፡፡

ሸ/ ማረሚያ መምሪያው ከውስጥ ገቢ በጀት ስራ ላይ ያዋሉትን የገንዘብ መጠን ልክ እንደ መደበኛ በጀት ሁሉ ገቢና ወጭ ሪፖርት በየወሩ ለኮሚሽኑና ለሚመለከታቸው ክፍሎች ያቀርባሉ ፣

1./የክልል ማረሚያ ኮሚሽኑ ከዞን ማረሚያ መምሪያ ከሚሰበሰብ ገቢ ከሚያገኝ ገቢ ድርሻ የሚከተሉ ተግባራት ያከናውናል

ሀ.ለተቋሙ የጋራ አገልግሎት ለሚሰጠው ተሽከርካሪጥገና አገልግሎት

ለ.የውስጥ ገቢውን ለማስፋት ለሚደረጉ የጥናትና ፣ የተሞክሮ ቅመራ ስራዎች ለማከናወን

ሐ.የውስጥ ገቢ አቅም ለማሳደግ ለሚከናወኑ የድጋፍ ክትትል ስራ

መ.ለአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ዕድሳት ጥገናና ግንባታ ስራ

ሠ.በማረሚያ ማዕከላት በመንግስት በአጋር አካላት በጀት የሚከናወኑ ፕሮግራምና ፕሮጀክቶችን ማስፈፀሚ ተቋማዊ የወጭ መጋራት ስራ በጀት ድርሻ በመወሰን ፕሮግራምና ፕሮጀክቶትን እንድፈፀሙ ማድረግ

ረ..ለተቋሙ አገልግሉት የሚሰጡ የተሽከርካሪ ግዥ

ሸ/ ከላይ ማከናውን የሚቻለው የኮሚሽኑ የገቢ አቅም እስከ ፈቀደ ድረስ ይሆናል

2./በኮሚሽንና በዞን ማረሚያ መምሪያ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ አጠቃቀም ስርዓቱን የሚመሩየጋራ አመራር ኮሚቴ ይደራጃል

ሀ.በክልል ማረሚያ ኮሚሽን ደረጃ የውስጥ ገቢ አስተዳደሩ በኮሚሽኑ ማኔጀመንት ይሆናል

ለ.በዞን ማረሚያ መምሪያ ደረጃ የውስጥ ገቢ አስተዳደሩ በመምሪያ የማኔጅመንት አባላት እና የታራሚ ህግ ታራሚዎችን ከሚወክሉ አብይ ኮሚቴ የጠቅላላ ኮሚቴ ሊቀ-መንበር ፤ፀሐፊና የውስጥ ቁጥጥር ኮሜቴ የጋራ አመራር ኮሚቴ ሆኖ በጋራ ይሰራል ።

3./ የህግ ታራሚዎች ጠቅላላ ኮሚቴዎች ተሳትፎ የለለበት የውስጥ ገቢ አመራርና አስተዳደር ስርዓት ልኖር አይገባም የበጀት እቅዱ ሲፀድቅ የጋራ ውሰኔ በቃለ -ጉባኤ ተደግፎ መቅርብ ይኖርባታል ፣

4/ የዞን ማረሚያ መመሪያዎች በበጀት ዓመቱ በውስጥ ገቢ ለሚከናወኑ በዕቅድ ላቀመጡት ስራ ማስፈፀሚያ የሚያቀርቡት የበጀት ፍላጎት ጥያቄ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ለኮሚሽኑ ቀርቦ ኮሚሽኑ የቀረበውን የስራ ዕቅድ እና የበጀት ፍላጎቱን በዝርዝር በመገምገም በጀቱን ሲያፀድቅ በጀቱን የሚጠቀሙ ሲሆን ኮሚሽኑ ከዞን የቀረበ የበጀት ጥያቄ በ10 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በጀቱን አፀድቆ ለዞኑ ማሳወቅ አለበት ።

5/ የክልሉ ማረሚያ ኮሚሽን ከዞን ማረሚያ መምሪያ ከሚያገኝ የገቢ ድርሻ በበጀት ዓመቱ በውስጥ ገቢ በጀት የሚያከናውን ስራዎችን በዕቅድ ማስቀመጥ ዕቅዱን በገምግሞ በማፅደቅ በጀቱ በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ እንዲሆን ያደረጋል በበጀት ዓመቱ በውስጥ ገቢ ለማከናውን ዕቅድ የተቀመጡ ተግባራትን ለዞን ማረሚያ መምሪያዎች ያሳውቃል

6.ኮሚሽኑእና የዞን ማረሚያ መምሪያ ከውስጥ የሚያገኙት የገቢ ድርሻ የፋይናንስ አሰራርን ተከትሎ ስራ ላይ የሚያውሉ ይሆናል ፡፡

7./በውስጥ ገቢ የማይሸፈኑ ወጭዎች ማረ/ቤቶች የውስጥ ገቢአቸውን ከዚህ በታች ለተመለከቱት ተግባራት ማዋል አይፈቀድላቸውም ፡፡

ሀ. ለወጭና ለሀገር ውስጥ ለሠራተኞች የሚሰጥ ት/ት ስልጠና ወጭ

ለ. ለታራሚዎች ምግብ

ሐ. ለፖሊስ አባላትና ስቨል ሠራተኞች ደመወዝ

መ. ለአባላት ደንብ ልብስ ግዥ ማዋል አይቻልም

**20.የገቢ ሂሳብ አመዘጋገብ ፣**

1. የእየዕለቱ የሂሳብ እንቅስቃሴ የጥንድ ሂሳብ አያያዝ ስርዓቱን በተከተለ ሁኔታ ተፈጻሚይሆናል ፣
2. ማንኛውም የሂሳብ እንቅስቃሴ የፋይናንስ ህግን የተከተለ መሆን አለበት ፣

**21./የውስጥ የገቢሂሳብ አያያዝ አመዘጋገብና ሪፖርት አቀራረብ ፤**

1. የዞን ማረሚያ መምሪያ በየወሩ ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበውን የገንዘብ አጠቃቀማቸውን ለክልል ማረ/ቤቶች ኮሚሽን ሪፖርት የሚያቀርብ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ እና ለሚመለከታቸው አካለት እንዲቀርብ ይደርጋሉ ፣
2. የዞን ማረሚያ ወርሃዊ የወጭ ሪፖርት ለሚመለከታቸው ክፍሎችና ኃላፊዎች ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባሉ ፣
3. የክልል ማረሚያ ኮሚሽን ከዞን ማረሚያ መምሪያ የሚቀርብ ወቅታዊ የውስጥ ገቢ ሪፖርት መነሻ በማድረግ የገቢ አስተዳደር ሂደት ላይ ክትትል ያደርጋል
4. በዞን ማረሚያ መምሪያዎች ተግባራዊ እንዲሆን የተቀመጡ የሂሳብ አሰራሮች በሙሉ በክልሉ ማረሚያ ኮሚሽን ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል ወይም ይከናወናሉ ፣
5. የክልሉ ማረሚያ ኮሚሽን የገቢ በጀት አጠቃቀም ሪፖርት በማዘጋጀት ከዞን ማረሚያ መምሪያ የገቢ አጠቃቀም ሪፖርት ጋር በመገምገም ያሉ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት

በአፈፃፀሙ ላይ የታዩ ክፍተቶ ካሉ የማስተካከያ አቅጣጫ በማስቀመጥ ግብረ- መልስ ይሰጣል አፈፃፀሙን ይከታተላል

6. በዞን ማረሚያ መምሪያ የውስጥ ገቢ አስተዳደሩ ከመደበኛ በጀት ጋር የውስጥ ገቢን ለማስተዳደር የተቀመጠ የአሰራር መመሪያና መደበኛ የፋይናንስ አስተዳደር ተከትሎ በመምሪያው ፋይናንስግዥ ዳሬክቶሬት ስር የሚመራ ሆኖ የበጀት እንቅስቃሴ ራሱን በቻለ መደብ ያለው ሲሆን የውስጥ ገቢ ሂሳብ የሚመሩ የራሱ የሂሳብ ባለሙያ ፤ገንዘብ ያዥ ፤ግዥ እና ንብረት ኦፌሰር እንዲኖረው ይደረጋል
7. የውስጥ ገቢ የገንዘብ ወጭ ትዕዛዝ ጥያቄ በመምሪያ የታራሚ ማረም ማነፅ የስራ ሂደት አስተባባሪ/ዳይሬክቶሬት /በኩል ሲቀርብ የቀረበ የወጭ ትዕዛዝ ጥያቄ በመምሪያ ዕቅድ ዳሬክቶሬት የወጭ ጥያቄ በውስጥ ገቢ ለማከናውን በዕቅድ የተያዘ ስራ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሲሰጥበት ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል
8. የክልል ማረሚያ ኮሚሽን ከውስጥ ገቢ የሚያገኝ የገቢ ድርሻ ለዚሁ ዓላማ በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ቁጥር የሚቀመጥ ሲሆን ከዞን ማረሚያ ወደ ኮሚሽን በባንክ የተላከ ገንዘብ በክልል የገቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ ይደረጋል
9. በክልል ገቢ ሂሳብ የተመገበ በጀት በበጀት ዓመት በውስጥ ገቢ ለመስራት የተቀመጠውን ዕቅድ መሰረት በሂሳብ መለያ መደብ ቁጥር 1441 ተመዝግቦ አስፈላጊ በሆኑ የወጭ አርዕስት ተደልድሎ ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል
10. ኮሚሽኑ ከውስጥ ገቢ ከሚያገኝ የገቢ ድርሻ በጀት በበጀት ዓመቱ ለማከናውን በዕቅድ የተቀመጠ ዕቅድ ለማሳካት ከአሠራር አንፃር የውስጥ ገቢውን በፑል አሰራር ለመምራት ምቹ ሁኔታ ባለመኖሩ ተቋማዊ አደረጃጀት ማሻሻያ እስክ ደረግ ድረስ ካለው የሰው ኃይል የስራ ጥራትና ብቃት ያለው ባለሙያዎች በአመራር ኮሚቴ በመለየት------ ተጠሪ የሆኑ **የሂሳብ ባለሙያ ፤ገንዘብ ያዥ እና የግዥ**ባለሙያዎችን በመመደብ የገቢ አስተዳደር ስርዓቱ ግልፅና ተጠያቂነት ባለው አሰራር እንድመራ ያደርጋል

## ክፍል አራት

22..**የውስጥ ገቢ የጋራ አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት** ፦ የውስጥ ገቢበአግባቡ ማስተዳደር የሚያስችል ኮሚቴ በክልል በዞን ማረሚያ ቤቶች ይቋቋማል ፤የኮሚቴው ጥንቅር ፤ተግባር እና ሀላፊነት

1. የማረሚያ ቤቶች የውስጥ ገቢ አሰባሰቡ እና አጠቃቀሙን የሚወሰን የጋራ አመራር ኮሚቴ በየደረጃው ይቋቋማል ፣
2. የጋራ አመራር ኮሚቴው ከማረሚያ ቤቱ የማኔጅመንት ኮሚቴ እና ከታራሚዎች ጠቅላላ አመራር ኮሚቴዎች የተወጣጣ ይሆናል ፣
3. በየደረጃው የሚቋቋመው የማረሚያ ቤቶች የጋራ ኮሚቴ ተጠሪነቱ በክልሉ ደረጃ ለኮሚሽነሩ ሲሆን በዞን ማረሚያ ቤት መምሪያ ለዞኑ መምሪያ ኃላፍ ይሆናል ከ---- ብር በላይ የሆነ ውሳኔ ስኖር ለክልሉ ማረሚያ ቤት የውሳኔ ሀሳብ ቀርቦ በኮሚሽኑ በኩል ውሳኔ ስሰጥበት ስራ እንዲውል ይደረጋል ፡፡

**23 የኮሚቴው አባላት ቁጥር ከ---- እስከ --- ይሆናል ፣**

**24.የኮሚቴ አባላት ስብጥር ፣**

ሀ.የክልሉ ማ/ቤቶች ኮሚሽን ኮሚሽኔሩ ሰብሳቢ ሆኖ የኮሚሽኑ ----- የስራ ክፍሎት አባል ይሆናሉ

ለየዞን ማረሚያ መምሪያ ኃላፊ ሰብሳቢ ፣------- የስራ ክፍሎች አባልሆኖ የታራሚ አይብ ኮሚቴ ሊቀ-መንበር ፣ፀሐፍ ፣ቁጥጥር ኮሚቴየኮሚቴው አባላት አባል ሆኖ ይሰራሉ ፡፡

**25.የማረሚያ ኮሚሽን የውስጥ ገቢ አስተዳደር/አመራር ኮሚቴ/ ተግባርና ኃላፊነት**

1. የዞን ማ/ቤቶች ገቢ የመሰብሰብ አቅማቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ማ/ቤቶች በዓመት የሚሰበሰቡትን የገቢ መጠን በመወሰን በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የዞን ማ/ቤቶች ድርሻ ያሳውቃል ፡፡
2. የዞን ማረሚያ መምሪያ የሚሰበሰቡትን ገቢ በመጠቀም በአመቱ በውስጥ በውስጥ ገቢ ለሚሰሩትን የታቀዱ የስራ ዕቅድና የበጀትፍላጎቻውን በመገምገም በበጀት ዓመቱ ከውስጥ ገቢ የሚጠቀሙትን ጥቅል በጀት በማፅደቅ ለዞን ማረሚያ ቤት ያሳውቃል ፡፡
3. ኮሚሽኑ አማራጭ የስራ መስኮችን ለማስፋት የተቋሙን የገቢ አቅም ማሳደግ የሚያስችሉ አማራጭ የስራ መስኮችን ለማስፋት ተሞክሮችን በመቀመር
4. ከሚሽኑ ከዞን ማረሚያ ቤት ጋር በመቀናጀት አማራጭ የገቢ ማስገኛ ስራ መስኮችን በማጥናት በዞን ማረሚያ ቤት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል ፡፡

5. ኮሚሽኑ  በዞን ማ/ቤቶች ከሚሰበሰብ ገቢ በሚያገኘው የበጀት ድርሻ በማሰባሰብ ከዞን ማረሚያ ቤት መካከል በጥናት ላይ የተመሰረተ ቅድሚያ ልሰጡ የሚችሉ የት/ት፤የስልጠና ፤የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ፤የውስጥ ግብዓት አቅርቦት ማሚያ ተግባራት ላይ እንዲውል ያደርጋል ፡፡
6. በተቋሙ የሚከናወኑ የካፒታል ፕሮጀክት ፕሮግራሞች ማስፈፀሚ የተቋሙ ወጭ ድርሻ በመወሰን ለመንግስት የበጀት ጥያቄ በማሳወቅ የውስጥ ፋሲሊትና መሰረተ ልማት ስራስራዎች በአግባቡ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል ፡፤
7. በዞን ማ/ቤቶች ከውስጥ ገቢ በጀት የሚሰሩ የግንባታ እና ልዩ ልዩ ስራዎች አፈጻፀምን ይከታተላል ይቆጣጠራል፡፡
8. የውስጥ ገቢ በጀት አሰባሰብና አጠቃቀም ስርዓቱ የፋይናንስ የአመራር መመሪያዎችን መሰረት አድርጎ ተግባራዊ እንዲሆኑ የኦዲትና ኢንስፔክሽን ስራዎችን ተግባራዊ እንዲሆን ከማድረግ በተጨማር በውስጥ ገቢ አስተዳደር ስርዓቱ ላይ አጠራጣር የሆኑ ጉዳዮች ሲኖሩ በክልሉ በዋና ኦዲት መ/ቤት በኩል የኦዲት ስራ  እንዲካሄድ ያደርጋል፡
9. በዞን ማ/ቤቶች የገቢ ማስገኛ የስራ መስኮችን በመለየት መረጃውን በአግባቡ ተደራጅቶ እንድይዙ ይደረጋል፡፡
10. ከመደበኛ ዕቅድ አፈፃፀም በተጨማሪ የውስጥ ገቢ አፈጻፀም ሪፖርቶችን በመገምገም የቀጣይ አቅጣጫ እንዲቀመጥ ያደርጋል ፡፡
11. ከዞን ማ/ቤቶች ከሚገኙ የህግ ታራሚዎችን አማራጭ የስራ መስክ አቅርቦ በውስጥ ገቢ የብድር ጥያቄ የሚያቀርቡት ታራሚዎችን ያቀረቡትን ስራ አማራጭ በመገምገም ከማህበራት ካፐታል መጠን የ---- ፐርሴንት ድርሻ የብድር አገልግሎት እንዲሰጣቸው ይወስናል ከማረሚያ ቤት ብድር የተሰጣቸው ታራሚዎች የተበደሩበት ብድር ---- ጊዜ ውስጥ ገንዘብን ተመላሽ ለማድረግ በህግ ፍትህ የሚፀና ውል በመፈራረም ብድሩን እንዲያገኙ ይደረጋል ፡፡
12. የውስጥ ገቢ አቅም ታሳቢ በማድረግ የገቢ አስተዳደር ስርዓቱ በተደራጀ አግባብ እንዲመራ በክልልና በዞን ማረሚያ የፋይናንስ አስተዳደሩን የሚመራ ሰው ኃይል አደረጃጀት በማጥናት አደረጃጀቱ ተግባረዊ እንዲሆን ያደርጋል
13. የውስጥ ገቢ የአሰባሰብና የአጠቃቀም ስርዓትን ይከታተላል የቆጣጠራል በአፈፃፀም ሂደት የሚታዩ የሚታዩ ክፍተቶችን በጥናት በመለየት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል

14.የተቋሙን የዕድገት አቅጣጫ መሰረት በማድረግ የውስጥ ገቢ አስተዳደር ስርዓቱን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በአሰራር መመሪያው እንዲሻሻል ያደርጋል

**26.የዞን ማረሚያ መምሪያ ኮሚቴው አባላት ተግባርና ኃላፊነት ፣**

1. የአመቱን የውስጥ ገቢ እቅድ ያዘጋጃል ፣ሲፀድቅም ለማረሚያ ቤቱ ሠራተኞች እና ለታራሚዎች አቅርቦ ያወያያል ፣ በተዘጋጀው እቅድ መሰረት ገቢው መሰብሰቡን ይከታተላል ፣ ይቆጣጠራል ፣
2. የተሰበሰበውን የውስጥ ገቢ አጠቃቀም እቅድ ያዘጋጃል ፣በእቅዱ መሰረት ተግባራዊ መሆኑን ይቆጣጠራል
3. የተዘጋጀውን የገቢ እና የአጠቃቀም እቅድ ለክልሉ ይልካል ፣
4. የውስጥ ገቢው የተቋሙን የጥበቃ ፣የታራሚዎች አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል ፣ለታራሚዎች የባህሪ ለውጥ ሊያመጣ በሚችል ተግባር ላይ መዋሉን ይከታተላል ፣ የገቢ አቅም እንዲያድግ ጥረት ያደርጋል ፣
5. የዞን ማረሚያ መምሪያ አስቸኳይ /ድንገተኛ የሆነ ጉዳይ ሲያጋጥሚ በዞኑ መምሪያ ኃላፊውሳኔ እስከ ብር 30,000.00/ሰላሳ ሺህ ብር / ገንዘብ ወጭ ማድረግ የሚቻል ሲሆን በኃላፊ ትዕዛዝ ወጭ ውሳኔው 15 ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ገንዘቡ ወጭ የተደረገበት ምክንያት ለጋራ አመራር ኮሚቴ ቀርቦ በጉዳዩ ላይ የጋራ መግባባት ስፈጠርበት በቃሌ ጉባኤ እንዲፀድ ይረጋል
6. ኮሚቴው በግል እና የጋራ ተጠያቂነት ይኖርበታል ፣
7. ከሙስና እና ከብክነት የፀዳ አሰራር እንዲኖር ስልት ይቀይሳል ፣
8. ኮሚቴው በየወሩ የስራ አፈጻፀሙን ይገመግማ ፣ በየሦስት ወሩ እቅድ እና የእቅድ አፈጻፀሙን ፣የተገመገመውን ሪፖርት ለክልል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ይልካል፣
9. የየኮሚቴው ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ይሆናል ፣ ድምጹ እኩል በእኩል የሆነ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ድምጽ አብላጫ ይሆናል ፣ ለልዩነት በቃለ -ጉባኤ ይመዘገባል ፣
10. የኮሚቴው ውሳኔ በቃሌ ጉባኤ መያዝ ይኖርበታል ፣

**27.የዞን ማረሚያ መምሪያ ኃላፊው ኃላፊነትና ተግባር ፣**

1. የውስጥ ገቢውን አሰባሰብ ሂደት በበላይነት ይመራል ይከታተላል ፣

2. በውስጥ ገቢ የሚሰሩ ስራዎች ለጋራ አመራር ኮሚቴ በማቅረብ የስራ ፕሮግራምና የበጀቱ የጋራ ውሳኔ በማስቀመጥ ስራዎች እንዲሰሩ ያደርጋል
3. የወጭ አጠቃቀሙን ስርዓቱ በየወሩ ለጋራ አመራር ኮሚቴው ቀርቦ እንዲገመገም ያደርጋል ፣
4. የውስጥ ገቢ የወጭና ገቢን ስርዓትን ያስተዳድራል ፣ይመራል ፣ይቆጣጠራል ፣
5. ማንኛውም የገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም የፋይናንስ ደንብ እና መመሪያ የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል ፣ ኃላፊነትም ይወስዳል ፡፡
6. በሦስት ሰዎች ፈራሚነት ገንዘቡ ከባንክ እንዲቀሳቀስ ደርጋል ፡፡
7. የማ/ቤቱ ኃላፊ የመንግስት መመሪያን ከመተግበር አንፃር ከፋይናንስ አሰራር በግዥ ሂደት በንብረት አስተዳደር የሚፈፀሙ ተግባራትን ይከታተላል ይቆጣጠራል ፡፡

**28.ልዩ ልዩ ምርት ተመን ፣ አሻሸጥና የሽያጭ ገቢ አደራረግ**

ማ/ቤቶች የሚያመርቷቸውን ልዩ ልዩ ምርቶች በሚከተለው መልኩ ለሽያጭ ማቅረብ ይኖርባቸዋል

ሀ/ ምርቱ ለሽያጭ ከደረሰ በሚመለከተው የልማት አስተባባሪ መግለጫ ይቀርባል ፣ መግለጫው ለገበያ ጥናት ኮሚቴ በመምራት የገበያ ጥናት ያካሄዳል፡፡

ለ/ ምርቱ በሚመለከታቸው ኮሚቴዎች ከማሳ ፣ እንዲመጣ ይደረግና ተመዝኖ ይተመንና በሞዴል 19 ገቢ ይደረጋል፡፡

ሐ/ የተተመነው ምርት በሞ/22 ወጪ ሆኖ በሽያጭ ባለሙያ ሽያጭ ይከናወናል ፡፡

መ/ የተሸጠው ምርት ገንዘብ በዕለቱ ገቢ መደረግ አለበት ፡፡

ሠ/ ሳይሸጥ የተመለሰና የተበላሸ ምርት ካለ ለምርት ሽያጭ ኮሚቴ ውሳኔ ከተሰጠበት በኃላ በማቀናነሻ ፎርም በኮፒ ተሰርቶ የሚመለከተው የስራ ክፍል አፅድቆት አንደኛው ከገቢ ደረሰኙ ጋር ይያያዛል ፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ድንጋጌ

**29.ጥፋቶችና ቅጣቶች**

1. የክልሉ ማረሚያ ኮሚሽን የውስጥ ገቢው አሰተዳደር ስርዓት በየጊዜው በውስጥ ኦዲት አማካኝት ኢንስፔክሽንና ኦዲት ስራ ተግባራዊ እንዲደረግ ያደርጋል፡፡

2. የኢንስፔክሽንና የውስጥ ኦዲቱ ውጤቱ የሂሳብ አሰራር እና የገንዘብ ብክነት ችግር ያለ ስለመሆኑ አመላካች ጉዳይ ሲኖር በክልሉ ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ጥያቄ አቅራቢነት በህግ ስልጣን ባለው በክልሉ ኦዲት ቢሮ በኩል ኦዲት እንዲደረግ ያደርጋል ፤

3. የውስጥ ገቢው ለማስተዳደር ከተቀመጠ ድንጋጌ ወጭ የውስጥ ገቢ በጀቱን ለለላ ዓላማ ማዋል ፤ከውስጥ ገቢ በጀት ለገለሰቦችም ለተቋማት ብድር መስጣት የተከለከለ ነው

4.ይህን መመሪያ ለማስፈፀም በማናቸውም ደረጃ በተቋሙ የተሾመ ወይም የተመደቡ ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ከፊደል ሀ እስከ ሐ ያሉ ጉዳዮችን የመፈፀምና የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት ፤

ሀ/ የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም አሰራርን በማጭበርበር ወይም በሌላ ሰው እንዲጭበርበር በማመቻቸት የተባበረ ፤

ለ/ ይህን የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ከፋይናንስ ደንብና መመሪያ የጣሰ ወይም በሌላ በማንኛውም ሰው እንዲጣስ ሆን ብሎ የፈቀደ ፤

ሐ/ በፍቃድኝነት በማንኛውም መንገድ ሀሰተኛ ሰነድ ላይ የፈረመ ወይም የመዘገበ በዲሲፕሊን የሚወሰደው ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ በማጭበርበርና በእምነት ማጉደል በገንዘብና ንብረት ማጥፋና ለግል ጥቅም ማዋል ወንጀል ክስ ተመስርቶበት እንዲቀጣ ይደረጋል ፡፡

4./ የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ መመሪያዎች ይህን መመሪያ የሚቃረኑ ማናቸውም መመሪያ ወይም የተለመደ የአሰራር ልምድ በዚህ ለሦስተኛ ዙር ተሻሻሎ በወጣው የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም ፡

**30/ መመሪያ ስለማሻሻል**

የቤ/ጉ/ክ/መ/የማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ይህ መመሪያ መሻሻል አለበት ብሎ ባመነ ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል ፡፡

**31.መመሪያው የሚፀናበት ቀን**

ይህ መመሪያ በክልሉ ማረሚያ ኮሚሽን በኮሚሽነሩ ፀድቆ ከወጣበት ቀን -------------2017 ዓ/ም ተፈፃሚ

------------ቀን 2017 ዓ/ም

መለስ በየነ አብሾኮ

አቶ

የማ/ቤቶች ኮሚሽን ኮሚሽነር